የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 17
ADDIS ABABA - 5th February, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፯፻፲

## CONTENTS

Proclamation No. 270/2002
Providing Foreign Nationals of Ethiopian Origin with certain Rights to be Exercised in their Country of Origin Proclamation ................................ Page 1710

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬

## የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ በርካታ የውጭ ዜጎች ከትውልድ አገራቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚፈልጉ መሆናቸውን በመገንዘብ ፤

እነዚህ የውጭ ዜጎች ተለይተው አንዳንድ የመብት አጠቃቀሞችን የሚመለከቱ የሕግ ገደቦች ቢነሱላቸው ለሀገሪቱ እድገትና ለወገኖቻቸው ኑሮ መሻሻል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ በመታመኑ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩· አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## *PROCLAMATION NO. 270/2002*

## *A PROCLAMATION TO PROVIDE FOREIGN NATIONALS OF ETHIOPIAN ORIGIN WITH CERTAIN RIGHTS TO BE EXERCISED IN THEIR COUNTRY OF ORIGIN*

WHEREAS, a significant number of foreign nationals of Ethiopian origin wish to strengthen their tie with their country of origin;

WHEREAS, it is believed that foreign nationals could contribute to the development and the prosperity of the peoples and country of their origin if the legal restrictions pertaining to the enjoyment of certain rights and privileges are lifted;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby prolaimed as follows:

### PART ONE
### *General*

1. *Short Title*
   This Proclamation may be cited as "Providing Foreign Nationals of Ethiopian Origin with certain Rights to be Exercised in their Country of Origin Proclamation No.270/2002."

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

፩· "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ ማለት" ፣ የሌላ ሀገር ዜግነት ከመያዙ አስቀድሞ የኢትዮጵያ ዜግነት የነበረው ፣ ወይም ከወላጆቹ ፣ ከአያቶቹ ወይም ከቅድመ አያቶቹ ቢያንስ አንዱ በማናቸውም ጊዜ የኢትዮጵያዊ ዜግነት ይዞ የነበረ የውጭ ዜጋ ሲሆን፣ የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራ ዜግነትን መርጦ የያዘ ሰውን አይጨምርም ፤

፪· "የኢትዮጵያ ሚስዮን" ማለት የኢትዮጵያ ኤምባሲ ፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ማለት ነው ፤

፫· "ሚኒስቴር" ማለት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማለት ነው ፤

፬· "ባለሥልጣን" ማለት የደህንነት ፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ማለት ነው ፤

፭· በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትን ጾታ ያካትታል ።

፫· የአዋጁ ዓላማ

የዚህ አዋጅ ዓላማ ፤

፩· በኑሮና በሕይወት አጋጣሚዎች እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች የሌላ አገር ዜግነት የወሰዱ የኢትዮጵያ ተወላጆች የሆኑትን በመለየት የኢትዮጵያ ዜግነታቸው በመቅረቱ የተጣለባቸውን የሕግ ገደቦች በማላላት የተለያዩ ባለመብቶችና ጥቅማ ጥቅሞች ባለቤቶች ማድረግ ፤

፪· የኢትዮጵያ ተወላጆች የሆኑ የውጭ ዜጎች ለወገኖቻቸው ኑሮ መሻሻል ፣ ለትውልድ ሀገራቸው ዕድገትና ብልጽግና የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማስቻል ነው ።

፬· የተፈጻሚነት ወሰን

በዚህ አዋጅ በክፍል ሁለት የተመለከቱት መብቶች ተፈጻሚ የሚሆኑት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪(፩) ትርጓሜ የሚሸፈን ሆኖ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት የተሰጠና የኢትዮጵያ ተወላጅ መሆኑን የሚገልጽ የጸና መታወቂያ ወረቀት ለያዘ የውጭ ዜጋ ነው ።

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዙ የውጭ ዜጎች መብቶችና ገደቦች

፭· መብቶች

በዚህ አዋጅ መሠረት የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ያለው ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ በዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩት መብቶች ተጠቃሚ ይሆናል ፤

፩· ወደ ኢትዮጵያ ለመግባትና ኢትዮጵያ ውስጥ ለመቆየትም ሆነ ለመኖር የመግቢያ ቪዛና የመኖሪያ ፈቃድ እንዲኖረው አይጠየቅም ፤

፪· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮(፪) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሥራ ፈቃድ እንዲያወጣ ሳይገደድ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥሮ መሥራት ይችላል ፤

፫· አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የውጭ ዜጎች የመብት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚገድበው ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንበትም ፤

2. *Definitions*

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1) "Foreign National of Ethiopian Origin" means a foeign national, other than a person who forfeited Ethiopian nationality and acquired Eritrean nationality, who had been Ethiopian national before acquiring a foreign nationality; or at least one of his parents or grand parents or great grand parents was an Ethiopian national;
2) "Ethiopian Mission" means an Ethiopian Embassy, a Permanent Mission or a Consulate;
3) "Ministry" means the Ministry of Foreign Affairs of Ethiopia;
4) "Authority" means the Authority for Security, Immigration and Refugees Affairs;
5) Provisions of this Proclamation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

3. *Objectives of the Proclamation*

This Proclamation shall have the following objectives:

1) By identifying foreign nationals of Ethiopian Origin who have acquired foreign nationality due to their life circumstances or other factors, entitle them to various rights and privileges by lifting the legal restrictions imposed on them when they lost their Ethiopian nationality;
2) In order to create a legal framework whereby persons of Ethiopian Origin fulfill their contribution to the development and prosperity of their country of origin.

4. *Scope of Application*

The rights and privileges provided for under part two of this Proclamation shall be applicable to a foreign national covered by Article 2(1) of this Proclamation, who hold a valid identity card obtained pursuant to Regulations issued herunder attesting that he is a foreign national of Ethiopian origin.

## PART TWO

## *Rights and Responsibilities of the Holder of the Identification Card of Foreign Nationals of Ethiopian Origin*

5. *Rights*

The holder of the Identification Card of foreign national of Ethiopian origin shall enjoy the following rights and privileges:

1) he shall not be required to have an entry visa or residence permit to live in Ethiopia;
2) without prejudice to Article 6(2) of this Proclamation, he shall have the right to be employed in Ethiopia without a work permit;
3) he shall not be subjected to the exclusion that applies to foreign nationals regarding coverage of pension scheme under the relevant pension law;

፬· የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵(፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ባለቤትነት በሚመለከት በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ ፫፻፺–፫፻፺፫ የተመለከቱት ገደቦች አይመለከቱትም ፤

፭· እንደ ሀገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር ከፈለገ በሀገሪቱ የኢንቬስትመንት ሕግ መሠረት ለሀገር ውስጥ ባለሀብት በተፈቀዱ የኢንቬስትመንት መስኮች መሳተፍ ይችላል ፤

፮· የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን በመጠቀም ረገድ በውጭ ዜጎች ላይ በሕግ ፣ በመመሪያ ወይም በአሰራር ልምድ የተጣሉ ገደቦችና የሚደረጉ ልዩነቶች አይመለከቱትም ።

፮· ገደቦች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተደነገገው ቢኖርም፣ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዘ የውጭ ዜግነት ያለው ሰው፣

፩· በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ መብት አይኖረውም ፤

፪· በማናቸውም የሀገር መከላከያ ፣ የሀገር ደህንነት ወይም በውጭ ጉዳይና መሰል የፖለቲካ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመደበኛነት ተቀጥሮ መሥራት አይችልም ።

## ክፍል ሦስት
## የኢትዮጵያ ተወላጆች የሆኑ የውጭ ዜጎች መታወቂያ ካርድ አሰጣጥ

፯· የመታወቂያ ካርድ

በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መብቶች፣ ጥቅማ ጥቅሞችና ሀላፊነቶች ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ የኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆኑ የውጭ ዜጎች የመታወቂያ ካርድ በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት ሊሰጣቸው ይችላል ።

፰· መታወቂያ ካርዱ ለማን እንደሚሰጥ

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪/፩/ የተመለከተውን መመዘኛ የሚያሟላ ማንኛውም ሰው የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ መሆኑን የሚገልጽ የመታወቂያ ካርድ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ መሠረት ማመልከቻ በማቅረብ የማግኘት ሙሉ መብት አለው ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም፣ ማንኛውም አመልካች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬/፪/ ፣ ፲፬(፫) ወይም ፲፬(፬) ውስጥ ከተጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ የሚመለከተው ከሆነ የመታወቂያ ካርዱ አይሰጠውም ።

፫· በዚህ አዋጅ መሠረት የኢትዮጵያ ተወላጅ መሆኑን/ዋን የሚገልጽ መታወቂያ ካርድ የተቀበለ/ች የውጭ ዜግነት ያለው/ላት ሰው የሌላ ሀገር ዜግነት ያለው/ላት ሚስት ወይም ባል የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ ሚስት/ባል መሆኑን ወይም መሆኗን የሚገልጽ የመታወቂያ ካርድ የማግኘት ሙሉ መብት አለው/ላት ። ይህ መብት የኢትዮጵያ ተወላጅ ከሆኑ የውጭ አገር ዜጎች ጋር ጋብቻ የፈጸሙ የኤርትራ ዜጎችንም ይጨምራል።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠውን የመታወቂያ ካርድ የያዘ/ች ሰው በዚህ አዋጅ የተጠቀሱት መብቶችና ግዴታዎች ይመለከቱታል።

4) without prejudice to Article 40(3) of the Constitution, the provisions of Articles 390-393 of the Civil Code shall not apply to persons of Ethiopian origin holding the Identification Card;

5) he shall have the right to be considered as domestic investor to invest in Ethiopia under Investment law.

6) restrictions imposed on foreign nationals regarding the utilization of Economic, Social, and Administrative Services shall not be applicable to foreign nationals of Ethiopian origin holding the Identification Card.

6. *Exception*

Notwithstanding Article 5 of this Proclamation, the holder of the Identification Card of foreign national of Ethiopian origin:

1) Shall have no right to vote or be elected to any office at any level of Government.

2) Shall have no right to be employed on a regular basis in the National Defence, Security, Foreign Affairs and other similar political establishements.

## PART THREE
## Issuance of Identification Card

7. *Identification Card*

An Identification Card shall be issued, in accordance with this Proclamation with a view to identifying foreign nationals of Ethiopian origin and oversee the enforcement of the rights, privileges and responsibilities of such individuals.

8. *Identification Card Eligibility*

1) Any person fulfilling the criteria set out under Article 2(1) of this Proclamation, shall have the right to be issued with an Identification Card attesting his Ethiopian Origin in accordance with the application to be submitted pursuant to the regulations to be provided under this Proclamation.

2) Notwithstanding Sub-Article (1), of this Article, a person shall be denied from obtaining the Identification Card on any one of the grounds set out under Article 14(2), 14(3) or 14(4) of this Proclamation.

3) A spouse of a foreign national of Ethiopian origin who possesses foreign nationality shall be entitled to apply for an Identification Card specifying that he or she is the spouse of a person holding the Identification Card of a foreign national of Ethiopian Origin. This provision shall also apply to spouses possessing Eritrean nationality.

4) A person with an Identification Card issued in accordance with Sub-Article (3) of this Arcticle shall enjoy the rights and privileges and be subject to the restrictions stipulated in this Proclamation.

፭· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠው የመታወቂያ ካርድ የሚያገለግለው የመታወቂያ ካርዱ በአንቀጽ ፲፫ መሠረት እስካልተመለሰ ወይም በአንቀጽ ፲፬ መሠረት እስካልተሰረዘ ድረስ ወይም ጋብቻቸው እስካልፈረሰ ድረስ ብቻ ይሆናል ።

፮· ዕድሜው ፲፰ ዓመት ያልሞላው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የተቀበለ የውጭ ዜግነት ያለው ሰው ልጅ፣ ሌላ መታወቂያ እንዲያወጣ አይገደድም ። ልጁ የመታወቂያ ካርድ ባወጣው ወላጁ/ወላጆቹ ፣ ካርድ ላይ ብቻ በመመዝገብ በዚህ አዋጅ የተጠቀሱት መብቶች ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል ።

፯· ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፮) የተመለከተው ቢኖርም ፣ ዕድሜው ፲፰ ዓመት ያልሞላው በዚህ አዋጅ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋን ትርጓሜ የሚያሟላ ማንኛውም ሰው የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ስለ አካለ መጠን ስላላደረሱ ሰዎች በሚደነግገው መሠረት ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ የሚወሰነውን ክፍያ በመክፈል በግሉ የትውልድ ኢትዮጵያዊነት መታወቂያ ካርድ ማውጣት ይችላል ።

፰· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪(፩) የኢትዮጵያ ተወላጅ ስለሆነ የውጭ ዜጋ የተሰጠ ትርጓሜ ቢኖርም፣ ሚኒስቴሩና ባለሥልጣኑ ሲያምኑበት በኢትዮጵያ ኗሪ ለሆኑ የውጭ አገር ዜጎች በልዩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ የኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆኑ የውጭ ዜጎች የተሰጡ መብቶችንና ጥቅሞችን መስጠት ይችላሉ ። አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል ።

፱· <u>የመታወቂያ ካርድ የሚሰጠው አካል</u>

መታወቂያ ካርዱን ከኢትዮጵያ ውጭ ለመስጠት ሥልጣን ያለው ሚኒስቴሩ ሲሆን፣ በሀገር ውስጥ ደግሞ ባለሥልጣኑ ይሆናል ።

፲· <u>መታወቂያ ካርዱ እንዲሰጥ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

የመታወቂያ ካርድ አሰጣጥ ሁኔታ አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል ።

፲፩· <u>መታወቂያ ካርዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ መታወቂያ ካርድ የማደሻ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል ።

፲፪· <u>ክፍያ</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጠውን መታወቂያ ለማግኘት እንዲሁም መታወቂያውን ለማሳደስ የሚከፈለው ክፍያ መጠን በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል ።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፲፫· <u>መታወቂያ ካርዱን ስለመመለስ</u>

፩· ማንኛውም የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዘ የውጭ አገር ዜግነት ያለው ሰው በማናቸውም ጊዜና ምክንያት መታወቂያ ካርዱን መመለስ ይችላል ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንዳለ ሆኖ ፣ የመታወቂያ ካርዱን የመለሰ ሰው ካርዱን በተጠቀመባቸው ጊዜያት የገባቸውን ውሎች ወይም ሌሎች ግዴታዎችን የማክበርና የመፈጸም ኃላፊነት አለበት ።

5) The Identification Card issued in accordance with Sub Article (3) shall only be valid until the Identification Card of the person of Ethiopian Origin is returned in accordance with Article 13 or canceled in accodance with Article 14 or upon dissolution of the marrige.

6) The children of the holder of the Identification Card of foreign nationals of Ethiopian origin who are under the age of 18 may not be required to have a separate Identification Card. They shall have the right to enjoy facilities granted in this Proclamation provided that they are specified as children in their parent (s) identification Card.

7) Notwithstanding Sub-Article (6), children under the age of 18 covered by the definition of "Foreign national of Ethiopian Origin" under this proclamation, may have the right to be issued with separate Identification Card upon application, taking into account the provisions of the Ethiopian Civil Code pertaining to minors.

8) Notwithstanding the provision of Article 2(1) of this Proclamation, when the Ministry and the Authority find it appropriate, they may jointly grant to foreign national residing in Ethiopia, rights and privileges accorded to Foreign National of Ethiopian origin. The details shall be prescribed by a directive.

9. *Authority Issuing the Identification Card*

The Identification Card shall be issued by the Ministry when abroad and by the Authority when in Ethiopia.

10. *Application for the Issuance of Identification Card*

A regulation providing the conditions for the granting of the Identification Card shall be issued following this Proclamation.

11. *Validity of the Identification Card*

The duration for the renewal of Identification Card issued in accordance with Article 8 of this Proclamation shall be specified by the Regulation.

12. *Fee*

The amount of fee payble to obtain the Identfication Card and its renewal shall be specified by the Regulation.

## *PART FOUR*
## *Miscellaneous Provisions*

13. *Return of the Identification Card*

1) Any person holding the Identication Card of foreign national of Ethiopan Origin may return such card at anytime without specifying the reason.

2) Notwithstatnding Sub- Article (1), of this Article the person who returned the Identification Card, however, shall be responsible to perform the contract or other obligations he entered into during the validity of the Identification Card.

፲፬· <u>የመታወቂያ ካርድ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ</u>

ሚኒስቴሩና ባለሥልጣኑ በጋራ ሲወስኑ የመታወቂያ ካርዱ ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊሠረዝ ይችላል ፤

፩· መታወቂያው የተገኘው ሌላ ሰው መስሎ በመቅረብ ወይም ስለራሱ ትክክለኛውን ነገር በመደበቅ ወይም የተሳሳተ ማስረጃ በማቅረብ ከሆነ ፤

፪· የመታወቂያው ባለቤት በሽብርተኝነት ወይም የተከለከሉ ዕጾችን ወይም የጦር መሣሪያዎችን በማዘዋወር ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ፤

፫· የመታወቂያው ባለቤት ከኢትዮጵያ ጋር በጦርነት ላይ ያለ አገር ዜጋ ከሆነ ወይም ይህን ዓይነቱን አገር በፈቃደኝነቱ የሚረዳ ሰው ከሆነ ፤

፬· የመታወቂያው ባለቤት ለሌላ አገር መንግሥት በመደበኛ ውትድርና ወይም በደህንነት ሥራ ማገልገሉ ከተረጋገጠ ፤

፭· መታወቂያውን ይዞ መቆየቱ ለሕዝብና ለአገር ጥቅም ተገቢ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ።

፲፭· <u>ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች ፤ ደንቦች ፤ መመሪያዎች ፤ ውሳኔዎች ወይም አሠራሮች ይህን አዋጅ በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ።

፲፮· <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው መሥሪያ ቤት ወይም ሰው ለዚህ አዋጅ ተግባራዊነት የመተባበር ግዴታ አለበት ።

፲፯· <u>ደንብና መመሪያ ስለማውጣት</u>

፩· ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል ።

፪· ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል ።

፲፰· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም·

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

14. *Conditions for the Cancellation of the Identification Card*

The Identification Card may be cancelled for one of the following reasons upon the joint decision of the Ministry and the Authority:

1) if the Identification Card was obtained by means of fraud, false representation, or concealment of any material fact; or
2) If the holder of Identification Card has been convicted for crime of terrorism or smuggling of narcotics or armament;
3) if the holder of Identification Card is a citizen of any country at war with Ethiopia or is found willingly helping such counrtry;
4) if the holder of Identification Card is proved to have served in the regular army or intelligence of another country;
5) if it is contrary to the public and national interest that the person should continue to hold the Identication Card.

15. *Inapplicable Laws*

Any Laws, regulations, directives, decisions or procedural practices shall not be applicable in so far as they are inconsistent with this Proclamation.

16. *Duty to Cooperate*

Any concerned office or person shall extend the necessary assistance in the implementation of this Proclamation.

17. *Regulations and Directives*

1) The Council of Ministers may issue Reguations necessary for the proper implemention of this Proclamation.
2) The Ministry may issue Directives necessary for the proper implementioan of this Proclamation.

18. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 5th day of February, 2002.

Done at Addis Ababa, this 5th day of February, 2002.

*GIRMA WOLDEGIORGIS*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE